የጉራጌ ዞን ገቢዎች መምሪያ
የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
እና
ጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት
የመጣኔ ጥናት ፣ ታክስ ትምህርት እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት

መካከል የተገባ

# የ 2015 በጀት ዓመት የሚዛናዊ ውጤት ተኮር ዕቅድ የአፈፃፀም ስምምነት ውል

ሐምሌ / 2014 ዓ.ም
ወልቂጤ

1. መግቢያ

የታክስ ፖሊሲ ዋና ዋና ዓላማዎች የመንግስት የወጪ ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችል ገቢ ለመሰብሰብ፣ የገቢ ክፍፍል ለማድረግ፣የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ለማስፈን፣ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት እና በማህበራዊ ግንኙነትና ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ ጠቀሜታ የሌላቸውን ምርቶች አጠቃቀም ለመቆጣጠር ወይም ለመገደብ ነው። ታክስ ከእያንዳንዱ ግለሰብ የየዕለት እንቅስቃሴ ጋር በእጅጉ የተቆራኘና ከነዋሪው ህብረተሰብ ተሰብስቦ ለራሱ መሰረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ማሟያ የሚውል የገንዘብ ምንጭ ነው።

መንግሥት ያለበትን ፊርጀ ብዙ ኃላፊነቶች በብቃት ለመወጣት የሚያስፈልገውን በጀት ለመሸፈን ያስችለው ዘንድ ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ሀብት ገቢ የመሰብሰብ ሙሉ የሥልጣን ውክልና ከህዝቡ ተቀብሏል። በዚሁ መሠረት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ቀልጣፋና ውጤታማ የሕዝብ ፋይናንስ አስተዳደር በመገንባት ለግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት መንግስትን ጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆም ከማድረጉም በላይ ለሕዝቡ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በሚያደርገው ጥረት ትልቅ ሚና ይጫወታል። በሌላ በኩል የታክስ ስርዓትና አስተዳደር የሚገኝበት ሁኔታ የአንድ መንግስት የመልካም አስተዳደር ቁልፍ መለኪያ ሆኖ ይወሰዳል።

በገቢዎች ባለስልጣን አምስት የትኩረት መስኮች ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ የአሰራር ልህቀትን ማረጋገጥ፣ ስትራቴጂያዊ አጋርነት ልህቀት ማምጣት፣ የህግ ተገዥነት አመራር ልህቀትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ የገቢ ዕድገት ማምጣት ተቋማዊ የተለዩ ሲሆኑ እነዚህን የትኩረት መስኮች ለማሳካት የሚያስችሉ አስራ አምስት ስትራቴጂያዊ ግቦች ተለይተዋል ።

ከተለዩት አስራ አምስት ስትራቴጂያዊ ግቦች የሚጠበቀውን ዉጤት ለማረጋገጥ ተቋሙ የሚከተላቸዉ ዋና ዋና አቅጣጫዎች ታክስን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህል ማሳደግ፣ ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓትን መገንባት፣ ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ፣ የዳበረ የሥራ ባህል መገንባት እና ስትራቴጂካዊ አጋርነትን ማጠናከር ናቸው ።

በ 2015 በጀት ዓመት 17.9 ቢሊዮን /አስራ ሰባት ነጥብ 9 ቢሊዮን/ ብር በመሰብሰብ የክልሉ ገቢ ለክልሉ አጠቃላይ ምርት /RGDP/ ያለውን ድርሻ 10.68% እንዲሁም ገቢው ለክልሉ ወጪ ያለውን ድርሻ 40.35% ለማድረስ እቅድ ተይዟል። ከዚህ ውስጥ በዞኑ የሚሰበሰብ ገቢ 2.30 ቢሊዮን በዕቅድ ዘመኑ የተያዘ ሲሆን እንደ በጌታ ወረዳ ደግሞ የሚሰበሰብ ገቢ **66.959** ሚሊዮን በዕቅድ ዘመኑ ለመሰብሰብ በዕቅድ ተይዟል።

## 2. የተቋሙ ተልዕኮ፣ ራዕይ ፣ ዕሴቶች እና የገቢ ዕቅድ፦

### 2.1 የተቋሙ ተልዕኮ

ሁለንተናዊ አቅሙ የተገነባ ተቋም እና የሰዉ ኃይል በማፍራት ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ የተጣጣመ ሀገራዊ እና ክልላዊ የታክስ አስተዳዳር ሥርዓት በመገንባት ፣ ፍትሀዊ፣ የላቀ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት አገልግሎት በመስጠት፤ ታክስ በፍቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር፤ የታክስ እና የገቢ ህግጋትን በማስከበር ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ መሰብሰብ"

### 2.2 ራዕይ

በ *2022* ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ስርዓት ተገንብቶ ኢኮኖሚዉ ከሚያመነጨዉ ሀብት ሙሉ በሙሉ ገቢ ተሰብስቦ ለልማት ዉሎ ማየት

## 2.3 ዕሴቶች

- አገልጋይነት
- አገልግሎትን በጊዜና በጥራት በመስጠት በልጦ መገኘት
- መስጠት
- ሙያና ክህሎትን ለተጨባጭ ውጤት መጠቀም /Professionalism/
- ታማኝነት
- ተጠያቂነት
- በትብብርና በዉድድር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት

## 2.4 በ 2014 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው ከሚያመነጨው ለመሰብሰብ የታቀደ ገቢ፦

- መደበኛ ገቢ ብር **60,275,632**
- ማዘጋጃ ቤት ገቢ ብር **6,683,878**
- ጠቅላላ ገቢ ድምር ብር **66,959,510**

# 3. የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነዱ ማብራሪያ

## 3.1 የስምምነት ሠነዱ አስፈላጊነት

የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል መፈራረም እንደ አሠራር ሥርዓት ተድርጎ ሲሠራበት መቆየቱ ይታወቃል። በ 2014 በጀት ዓመትም ይህ የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሲዘጋጅ ተቋማዊ ጠቀሜታ እንደሚኖረው የሚታመን ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረው ቀርበዋል።

- የአከባበቢው የገቢ አቅም እና በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ እየተሰበሰበ የሚገኘውን ገቢ መጠን በመለየት የአካባቢው ኢኮኖሚ የሚያመነጨውን ገቢ በወቅቱ በመሰብሰብ የውስጥ የፋይናንስ አቅማችንን በማጎልበት የክልሉን የገቢ ዕቅድ ለማሳካት፣
- የጋራ ተቋማዊ ግብ በመጣል አሳታፊና ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት ለጋራ ውጤት ተናብቦ ለመስራት፣
- የየአከባቢው አስተዳደር አካላት የተቋሙን ግቦች እንዲያውቁ፣ የተገባውን ግዴታና የተሰጠውን ኃላፊነት በመገንዘብ ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ለአፈፃፀሙ መሳካት አስፈላጊውን የሰው ሃይል፣ በጀት እና ሌሎች ግብአቶችን እንዲያሟሉ ለማድረግ፣
- በየደረጃው የሚገኙ የተቋሙ ሥራ አመራር አካላት፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ሠራተኞች የክልሉ መንግሥትና ሕዝብ የሰጣቸውን ኃላፊነትና ያለባቸውን ተጠያቂነት ተገንዝበው ግዴታቸውን በዕቅድ፣ በዕውቀትና በአግባቡ ለመወጣት እንዲቻል ለማነሳሳትና ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው በመንቀሳቀስ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለባቸው ለማስገንዘብ ነው።

## 3.2 የስምምነት ሰነዱ ዓላማ_

በበጀት ዓመቱ ሊተገበሩ የታቀዱ ተቋማዊ ስትራተጂያዊ ግቦችንና ከግቦቹ የሚጠበቁ ውጤቶችን በመለየት ዕቅድን በየደረጃው እስከ ፈፃሚ ባለሙያ ድረስ ቆጥሮ በመስጠትና ቆጥሮ በመረከብ መርህ መሠረት የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ተግባዊ በማድረግ ተቋማዊ የአሰራር ሥርዓት እና ተጠያቂነት በማስፈን ተቋሙን ውጤታማ ለማድረግ ነው፡፡

## 3.3 የሰነዱ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነድ የጉራጌ ዞን ገቢዎች መምሪያ የታክስ ትምህርት፣ ኮሙዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ እና የጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የመጣኔ ጥናት ፣ የታክስ ትምህርት እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ ጋር በመፈራረም ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን ከዚህ ሠነድ ተመሳሳይ ያለው ከወረዳው የጽ/ቤት ኃላፊ ጋር በመፈራረም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

4. የጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የመጣኔ ጥናት ፣ የታክስ ትምህርት እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት የ 2015 በጀት ዓመት የውጤት ተኮር ዕቅድ፤

| ተራ ቁጥር | ዕይታዎች | ክብደት በ % | ስትራቴጂያዊ ግቦች | ክብደት በ% | ዝርዝር ግቦች | ክብደት በ % | የሚጠበቁ ውጤቶች | መለኪያ | ዒላማ | ሥራው የሚፈፀምበት ጊዜ በሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | **1 ኛ ሩብ ዓመት** | **2 ኛ ሩብ ዓመት** | 3 ኛ ሩብ ዓመት | 4 ኛ ሩብ ዓመት |
| 1 | **ተገልጋይ** | 10 | የገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሻሻል | 2 | የማዘጋጃ ቤት ገቢ ጥናትና መመሪያ ዝግጅት ስርዓትን በማሻሻል ለገቢ አሰባሰብ የሕግ መሠረትና ውጤታማነትን ማሳደግ። | 0.5 | ያደገ ገቢ | በሚሊዮን | **66.95 9** | | | | |
| 2 | | | | | የታክስ ትምህርት እና የህዝብ ግንኙነት የአሠራር ስርዓትን በማሻሰሻል ለገቢ አሰባሰብ ውጤታማነትን ማሳደግ። | 1 | | | | | | | |
| 3 | | | | | የታክስ እና የአገልግሎት ቅሬታ አሠራር ስርዓትን በማዘመን (ፈጣንና ወቅታዊ ውሳኔ በመስጠት ገቢ እንዲሰበሰብ ማስቻል) | 0.5 | | | | | | | |
| 4 | | | የአገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ልህቀትን ማሻሻል | 8 | የማዘጋጃ ቤት ገቢ ጥናትና መመሪያ ዝግጅት አሳታፊነትነት በማረጋገጥ የአገልግሎት ዕርካታን ማሳደግ ። | 2 | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | የተገልጋይ እርካታ በመቶኛ | 91 | 91 | 91 | 91 | 91 |
| 5 | | | | | የታክስ ትምህርት እና ድጋፍ አሰጣጥ ውጤታማነትና ተደራሽነት በማስፋት የአገልግሎት ዕርካታን ማሳደግ ። | 2 | | | | | | | |
| 6 | | | | | የታክስ እና የአገልግሎት ቅሬታ በወቅቱና ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲያገኝ በማድረግ የአገልግሎት ዕርካታን ማሳደግ | 2 | | | | | | | |
| 7 | | | | | በባለስልጣኑ እና በሕብረተሰቡ መካከል መልካምና ጤናማ የሁለትዮሽ ግንኙነት በማስፈን አመኔታን ማሳደግ። | 2 | ሕብረተሰቡ በታክስ ተቋሙ ላይ ያለው አመኔታ | አመኔታ በመቶኛ | 91 | 91 | 91 | 91 | 91 |
| 8 | **ፋይናንስ** | 5 | የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሰደግ | 5 | የሀብት አያያዝ፣ አጠቃቀምና ውጤታማነት ማሳደግ። በበጀት አጠቃቀም ዙሪያ ተጠያቂነት ማረጋገጥ። | 5 | ውጤታማ የሃብት አጠቃቀም | የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የውስጥ አሰራር | 15 | የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ማስፈን | 15 | በ2014 በጀት ዓመት ያልተጠናቀቀ በሞዴል መመሪያ 41/2013 የመጣኔ ተመን ጥናት ማካሄድ እና የመጣኔ ተመን በመለየት ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለስምምነት ማቅረብ። | | የተጣጣመ የታክስ አስተዳደር ሥርዓት | የፀደቀ መመሪያ | | | | | |
| 10 | | | | | በ2014 በጀት ዓመት ያልተጠናቀቀ በሞዴል መመሪያ 49/2014 የመጣኔ ተመን ጥናት ማካሄድ እና የመጣኔ ተመን በመለየት ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ለስምምነት ማቅረብ። | 2 | | የፀደቀ መመሪያ | 3 | 3 | 3 | | |
| 11 | | | | | የመጣኔ ተመን ጥናት እና መመሪያ ዝግጅት ድጋፍና ስምምነት መስጠት። | 2 | | አስተያየ የተሰጠበት ረቂቅ መመሪያ | 3 | 3 | 3 | | |
| 12 | | | | | ተጠሪ ለሆኑ የአስተዳደር ዕርከን የክትትልና ድጋፍ ስርዓትን ማሻሻል። የግምገማ እና ግብረ-መልስ ስርዓት መቅረፅ። | 1 | | የሕግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን ተፈጻሚ ያደረጉ የአስተዳደር እርከኖች በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 13 | | | | | ምርጥ ተሞክሮ መቀመር እና ማስፋፋት። እንዲሁም የልምድ ልውውጥ ለሚመጡ አካላት ልምድ ማካፈል። | 1 | | የተሞክሮ አይነት በቁጥር | 2 | | 1 | | 1 |
| 14 | የውስጥ አሰራር | 15 | የታክስ ህግ ተገዥነት | | ለደረጃ "ሀ'' እና "ለ'' ግብር ከፋይ የክህሎት ሥልጠና ተደራሽነትን ማሳደግ። | 4 | ያደገ የህግ ተገዢነት | ተቀባይነት ያለው የሂሳብ መዝገብ የያዙ የደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 82 | 82 | 82 | 82 | 82 |
| 15 | | | | | ለደረጃ "ሀ'' እና "ለ'' ግብር ከፋዮች በየወሩ የቤት ለቤት ድጋፍን ማጠናከር። | 3 | | የደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋዮች ቁጥር | 13 | 13 | 13 | 13 | 13 |
| 16 | | | | | የክዕሎት ሥልጠና የተሰጣቸው የደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋዮች በቁጥር | 3 | | የደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋዮች ቁጥር | 13 | | 5 | 4 | 4 |
| 17 | | | አፈፃፀምን ማሻሻል | 15 | የፊት ለፊት ለግብር ከፋይ የሚሰጥ የታክስ ግንዛቤ እና የባህሪ ስልጠና ሽፋንን ማሳደግ። በፍቃደኝነት የሚከፈል የታክስ ድርሻን ማሳደግ። | 3 | | ግብር ከፋዮች ቁጥር | 732 | 183 | 183 | 183 | 183 |
| 18 | | | | | የትምህርትና ድጋፍ ስትራቴጂ መተግበር፣ ትምህርቱ ያመጣውን ፋይዳ በመገምገም ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ ማድረግ እንዲሁም ግብረ-መልስ መስጠት። | 2 | | ተጠሪ አስተዳደር ዕርከን በቁጥር | 1 | 1 | | | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | | 20 | የህዝብ ግንኙነት እና ተቋማዊ ገጽታ ግንባታ ማሻሻል | 20 | ደረሰኝ ጠየቆ የሚገበያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በመቶኛ | | 2 | የተገነባ ተቋማዊ ገጽታ | በመቶኛ | 55 | 55 | 55 | 55 | 55 |
| 20 | | | | | በሚኒ ሚዲያ የተላለፈ መልዕክት | | 2 | | በቁጥር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 21 | | | | | በሞንታርቦ/ማይክራፎን የተላለፈ መልዕክት | | 2 | | በቁጥር | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 22 | | | | | ብሮሸር | በዓይነት | 1 | | በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 23 | | | | | | ስርጭት | 1 | | በቁጥር | 2000 | 500 | 500 | 500 | 500 |
| 24 | | | | | ህብረተሰቡ አዘውትሮ የሚጠቀምባቸው ዕቃዎች ላይ መልዕክት ማስተላለፍ | | 2 | | በቁጥር | 2 | | 1 | | 1 |
| 25 | | | | | ስቲከር | | 1 | | በቁጥር | 50 | 10 | 15 | 10 | 15 |
| 26 | | | | | ባነር | | 1 | | በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 27 | | | | | በራሪ ጹሁፍ | | 1 | | በቁጥር | 2000 | 500 | 500 | 500 | 500 |
| 28 | | | | | በተቋሙ ሶሻል ሚዲያ የተለጠፉ የግንዛቤ መልዕክቶች | | 2 | | በቁጥር | 24 | 6 | 6 | 6 | 6 |
| 29 | | | | | የሶሻል ሚዲያ ተከታዮችን ማብዛት | | 2 | | በቁጥር | 100 | 25 | 25 | 25 | 25 |
| 30 | | | | | የተካሄደ ዞናዊ  የገቢ ንቅናቄ | | 2 | | በቁጥር | 1 | | | 1 | |
| 31 | | | | | ለተለያዩ አደረጃጀቶች የተፈጠረ የግንዛቤ መድረክ በቁጥር፥ | | 1 | | በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 32 | | | | | በተቋሙ ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶችና ቅሬታዎች እንዲሁም ምላሽ፣ ማብራሪያና ማስተካከያ የሚሹ ጉዳዮችን በየጊዜው በመከታተል ተገቢዉ ምላሽ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ማድረግ፣ | | 1 | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 33 | | | | | በወቅታዊ አጀንዳዎች ላይ መግለጫ መስጠት፣ | | 1 | | በመቶኛ | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 34 | | | | | የህዝብ ግንኙነትና ተቋማዊ ገጽታ ግንባታ ሥራዎቹ ያመጡትን ለዉጥና ዉጤት በመገምገም ቀጣይነት ያለዉ የማሻሻያ እርምጃዎችን መዉሰድ። ግብረ-መልስ መስጠት። | | 2 | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 35 | የውስጥ አሰራር | | | | በኦዲት ግኝትና በመደበኛ የታክስ ውሳኔ ላይ የቀረበ ቅሬታ የአሠራር ስርዓትን ማዘመን። | | 4 | የላቀ የአሰራር ስርዓት | በስታንዳርድ መሠረት የታክስ ቅሬታ ምላሽ የተሰጣቸዉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 97 | 97 | 97 | 97 | 97 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | | 15 | የአሠራር ስርዓት አፈፃፀምን ማሻሻል | 15 | በአገልግሎት አሰጣጥ የሚቀርብ ቅሬታና አለመግባባት የማጣራትና የአፈታት ሥርዓት ማሻሻል። | 4 | | በስታንዳርድ መሠረት የአገልግሎት ቅሬታ ምላሽ የተሰጣቸዉ ግብር ከፋዮች በመቶኛ | 97 | 97 | 97 | 97 | 97 |
| 37 | | | | | በየደረጃው ምላሽ ያገኙ/ያላገኙ የታክስ እና የአገልግሎት ቅሬታ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ማሻሻል። | 3 | | የታክስ እና አገልግሎት ቅሬታ ውሳኔ አፈፃጸም ክትትል የተደረገባቸው ግብር ከፋይ በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 38 | | | | | የአገልግሎት አሰጣጥ የእርካታ ደረጃ ጥናት ሥርዓት ማሻሻል። | 4 | | የጥናት ሰነድ | 1 | | | | 1 |
| 39 | የውስጥ አሰራር | 10 | የባለድርሻ አካላት አጋርነትና ትብብር ማሻሻል | 5 | ከባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድና አፈጻጸም ውይይት፣የተለያዩ ስልጠና ስብሰባ ላይ ተሳትፎ በማድረግ አስተዋጽኦ ማበርከት። | 5 | የተፈጠረ ዉጤታማ ቅንጅታዊ አሰራር፤ የተፈቱ ችግሮች | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 40 | | | ተቋማዊ የዉስጥ ስጋት ስራ አመራርን ማሻሻል | 5 | በኦዲት እና ተቆጣጣሪ የተሰጠ ግብረ መልስ አፈጻጸም ማሻሻል። | 1 | የቀነሰ ተቋማዊ ስጋት | በኦዲት ግኝት የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 41 | | | | | መረጃን በአግባቡ ያለመያዝና ማዛበት የሚፈጸም የአሰራር ጥሰትን ማሻሻል። | 3 | | የስጋት ተጋላጭነት በቁጥር | 1 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 |
| 42 | | | | | የስነምግባር ግድፈት የመቀነስ አፈጻጸምን ማሻሻል። | 1 | | የስነ ምግባር ግድፈት በመቶኛ | 1.59 | 1.59 | 1.59 | 1.59 | 1.59 |
| 43 | መማማርና ዕድገት | 15 | የሰው ሀብት የመፈጸም ብቃት ማሳደግ | 15 | የስራ ተነሳሽነት ማሳደግ። የ 2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ከተጠሪ የአስተዳደር ዕርከን ጋር የዕቅድ ውል ስምምነት ማካሄድ። | 2 | የረካ ሰራተኛ፣ ምርታማነቱ ያደገ ሰራተኛ | በቁጥር | 1 | 1 | | | |
| 44 | | | | | የተከናወኑ ተግባራት በየሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት በማጠናከር ለዞን ማቅረብ። | 4 | | በቁጥር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 45 | | | | | የዕቅድ ውል ስምምነትና በአፈፃፀም ሪፖርት መነሻነት ለፈፃሚ የተሰጠ የቃል ወይም የጽሁፍ ግብረ መልስ | 2 | | በቁጥር | 2 | | 1 | | 1 |
| 46 | | | | | የሠራተኛውን እርካታና ምርታማነትን ለማሳደግ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ፡፡ ለፈጻሚዎችና ለዳይሬክቶሬቱ አስተባባሪዎች ሥልጣና መስጠት ወይም ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፡፡ በተለይ በአሰራር ማንዋል፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በህዝብ ግንኙነት፣ በጥናትና መመሪያ ዝግጅት እና በስልጠና አሰጣጥ፡፡ | 5 | | በዙር | 1 | | 1 | | |
| 47 | | | | | የምዘና እና የማበረታቻ ስርዓትን ማሻሻል፡፡ በየስድስት ወር የአፈፃፀም ምዘና በሥራ ዘርፍ፣ ዳይሬክቶሬት እና ፈጻሚ ደረጃ ማካሄድ፡፡ | 2 | | በቁጥር | 2 | | 1 | | 1 |
| | | 100 | 0 | 100 | 0 | 16 | | | | | | | |

ማሳሰቢያ፡- ቤት ለቤት ድጋፍ ያሉ በወረዳው ያሉ የደረጃ “ሀ” እና “ለ” ግብር ከፋዮች ቁጥር ለባለሙያዎች በማካፈል እያንዳንዱ ባለሙያ አፈፃፀም በሚገመገምበት ወቅት የግብር ከፋዮች ውጤታማነትን መሰረት እንዲያደርግ አፈፃፀሙ ሲለካ በዓመት አንድ ጊዜ ሳይሆን አንድ ግብር ከፋይ ቢያንስ በሩብ አመት አንዴ በድግግሞች በዓመት 4 ግዜ በመደገፍ ክፍተቱ እንዲያስተካክል ሊደረግ ይገባል፡፡

## 5. የአፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነዱን የተፈራረሙ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 5.1. የዞን የታክስ ትምህርት፣ኮሙዩኒክሽ እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት፤

- ☞ ፈጻሚው እና አመራሩ የሙያ ሥልጠናና ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ☞ የተመደበውን የዕቅድ ማስፈፀሚያ ሀብት ከብክነትና ከሙስና በመከላከል በቁጠባ ሥራ ላይ ማዋል፣
- ☞ ለሥራው አስፈላጊው የሆኑ በጀት እና ሎጅስቲክ ማሟላት
- ☞ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግና የአፈፃፀሙን ውጤታማነት ማሳደግ፣
- ☞ በየደረጃው የአስተዳደር እርከን የሚገኙ የአመራር አካላት የገቢዎች ጽ/ቤቶችን እንዲደግፉና ተቀራርበው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ☞ ወቅታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ መቀበል፣
- ☞ በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት የሚፈጠሩ የአሠራር እና ሙያዊ ክፍተቶች ሲያጋጥሙ ወቅታዊ የእርምት እርምጃ መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ፣
- ☞ በጽ/ቤቶች ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ወቅታዊ ግምገማ በማድረግ ግብረ-መልስ መስጠት።

### 5.2. የወረዳው የመጣኔ ጥናት ፣ የታክስ ትምህርት እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት፤

- ☞ ፈጻሚዎች የሙያ ሥልጠናና ሌሎች ተገቢ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ☞ የተመደበውን የዕቅድ ማስፈፀሚያ ሀብት ከብክነትና ከሙስና በመከላከል በቁጠባ ሥራ ላይ ማዋል፣
- ☞ የስምምነት ውል የተገባባቸውን ስትራቴጂያዊ ግቦች በውሉ መሰረት መፈፀምና ማስፈፀም፣
- ☞ ወቅታዊና ትክክለኛ የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፣
- ☞ መረጃ ሲጠየቅ ተአማኒነት ያለውና ትክክለኛ መረጃ በወቅቱ መስጠት፣
- ☞ ለክትትልና ግምገማ ሥራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- ☞ አግባብ የሆነን የሥራ መመሪያ መቀበልና በወቅቱ መፈፀም፣
- ☞ ከዞን የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ተፈራርመው የተረከቡትን ዕቅድ በተመሳሳይ መልኩ ከከተማው ጽ/ቤት ኃላፊ ጋር የአፈፃፀም ስምምነት ውል መፈራረም ናቸው።

### 5.3. የትግበራ ጊዜ

- ❖ ከሐምሌ 1/2014 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/2015 ዓ.ም

## 6. የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውሉን የተፈራረሙት አካላት

ይህን የዕቅድ አፈፃፀም ስምምነት ውል ሰነድ የተፈራረሙት የጉራጌ ዞን ገቢዎች መምሪያ የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ እና የጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የመጣኔ ጥናት ፣ የታክስ ትምህርት እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ ናቸው።

**6.1** የታክስ ትምህርት፣ ኮምዩኒኬሽን እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ

ስም ______________________________

ፊርማ __________________________ ማሕተም

ቀን __________________________

**6.2** በጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የመጣኔ ጥናት ፣ የታክስ ትምህርት እና ቅሬታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት አስተባባሪ

ስም ______________________________

ፊርማ ______________________________

ቀን __________________________

**6.3** የጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊ

ስም __________________________

ፊርማ __________________________ ማሕተም

ቀን __________________________